መልእክት አሥር

**ተስፋው፣ ትንቢቱ፣ ቅሬታው እና ምለሳው**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 25፡11፣ 29፡10-11፣ 14፤ 30፡1-3፣ 10-11፣ 16-19፤ 31፡1-9፣ 11-13፤ 33፡6

**I. እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች መርጦ እንደ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ሕዝቡ አደረጋቸው—ሮሜ. 9፡11-13፤ ሐዋ. 7፡38፦**

ሀ. በእግዚአብሔር እንደተመረጡ ሕዝቦቹ፣ ብዙ ሆነው ሳሉ አንድ የሆኑት የእስራኤል ልጆች ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናቸው—1 ቆሮ. 10፡1-11።

ለ. በዚህ ምሳሌ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር የተመረጠች እና የተዋጀች፣ ክርስቶስን እና መንፈስን እንደ ሕይወት አቅርቦት የምትደሰት፣ የእግዚአብሔርን መኖሪያ የምትገነባ፣ ክርስቶስን እንደ እድል ፈንታዋ የምትወርስ እንደሆነች፣ እንደምትዘቅጥ እና እንደምትማረክ፣ እንደምትመለስ እና የክርስቶስን መምጣት እንደምትጠባበቅ ማየት እንችላለን።

**II. ያሕዌ የእስራኤልን ምርኮ ለመመለስ እና ወደ ምድራቸው መልሶ ሊያመጣቸው ቃል ገብቷል—ኤር. 16፡15፤ 30፡1-3፣ 10-11፣ 1619፤ 31፡1-9፣ 11-13፦**

ሀ. "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም"—29፡11።

ለ. "በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ"—31፡3።

ሐ. "ምርኮአችሁንም እመልሳለሁ፣ ከአሕዛብም ሁሉ ዘንድ እናንተንም ካሳደድሁበት ስፍራ ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ እናንተንም ለምርኮ ወዳፈለስሁበት ስፍራ እመልሳችኋለሁ"—29፡14።

መ. "የእስራኤል ድንግል ሆይ፣ እንደ ገና እሠራሻለሁ አንቺም ትሠሪያለሽ፣ እንደ ገናም ከበሮሽን አንሥተሽ ከዘፋኞች ጋር ወደ ዘፈን ትወጫለሽ"—31፡4።

ሠ. "ይመጣሉ በጽዮንም ተራራ እልል ይላሉ፤ ወደ እግዚአብሔርም በጎነት፣ ወደ እህልና ወደ ወይን ጠጅ ወደ ዘይትም፣ ወደ በጎችና ወደ ላሞች ይሰበሰባሉ፤ ነፍሳቸውም እንደ ረካች ገነት ትሆናለች፣ ከእንግዲህም ወዲህ አያዝኑም"—ቁ. 12።

ረ. "ልቅሶአቸውንም ወደ ደስታ እመልሳለሁ፣ አጽናናአውማለሁ፣ ከኀዘናቸውም ደስ አሰኛቸዋለሁ"—ቁ. 13።

**III. ኤርሚያስ የእስራኤል ምርኮኛነት በባቢሎን ለሰባ ዓመታት እንደሚሆን ተነበየ—25፡11፦**

ሀ. የአገሩ እና የሕዝቡ፣ የመቅደሱ እና የከተማይቱ አሳዛኝ ሁኔታ ለሰባ ዓመት ብቻ እንደሚቆይ ለእርሱ በማረጋገጥ፣ ስለ ሰባ ዓመቱ የተነገረው ቃል ለኤርሚያስ መጽናናት ነበር—29፡10፤ ዘካ. 7፡5።

ለ. እግዚአብሔር ሕዝቡን ለምርኮ አሳልፎ እንደሰጠ እንዲሁ፣ እንደ ምርኮኞች ሳይሆን እንደ አሸናፊ ተዋጊዎች ይመልሳቸዋል—2ዜና. 36፡21-23።

ሐ. ዳንኤል ስለ ሰባ ዓመቱ የእስራኤል ምርኮ በኤርምያስ 25፡ 11-12 እና 29፡10-14 ያሉትን ትንቢቶች ስለተረዳ፣ ፊቱን "[ወደ ጌታ አምላኩ ይጸልይ ዘንድ]" አቀና—ዳን. 9፡2-3፦

1. በምድር ላይ እንዳለ የእግዚአብሔር አብሮ-ሠራተኛ ዳንኤል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከቃሉ ተረድቶ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በቃሉ መሠረት ጸለየ።
2. የእግዚአብሔር ውጥን ለኢየሩሳሌም መልሶ መገንባት የእስራኤልን ልጆች ወደ እስራኤል ምድር መመለስ እንደሆነ ዳንኤል ስላወቀ፣ ለዚህ ነገር ጸለየ፤ የእስራኤል ልጆች ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ እግዚአብሔር የዳንኤልን ጸሎት መፈፀሙ ነበር።

**IV. ያሕዌ የመንጋውን ቅሬታ ካባረራቸው ምድር ሁሉ ወደ በረታቸው ሰብስቦ ወደ መሰማሪያቸው እንደሚመልሳቸው እና እንደሚያፈሩ እና እንደሚበዙ ተናግሯል—ኤር. 23፡3፦**

ሀ. ከሰባው-ዓመት ምርኮ በኋላ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ከባቢሎን ወደ ቅድስቲቱ ምድር እንዲመለሱ ለመጥራት መጣ—25፡11፦

1. እግዚአብሔር ሕዝቡን እርሱ ወደ መረጠው ምድር እንዲመለሱ ሲጠራ፣ በጣም ጥቂቶች ምላሽ ሰጡ፤ ብዙኀኑ በምርኮኝነታቸው ቀሩ።
2. በቁጥር ጥቂቶች ብቻ ወደ ተመረጠው ምድር ተመልሰው መጡ፤ ቤተ መቅደሱን ለመገንባት ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት እነርሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅሬታዎች ነበሩ—ዕዝ. 1፡3፤ 2፡1-67።

3. እግዚአብሔር ከሰባ ዓመት የባቢሎን ምርኮ በኋላ ሕዝቡን ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመልስ ተስፋ ሰጥቶ ነበር (ኤር. 25፡11፤ 29፡10)፤ በዕዝራ እና በነህምያ መጽሐፍ ቅሬታው በዚህ የተስፋ ቃል መሠረት ተመለሰ።

ለ. እጅግ ብዙ እውነተኛ አማኞች ተበታትነው እና በምርኮ ውስጥ ቀርተው ሳሉ፣ ዛሬ በጌታ ምለሳ እኛ ወደ እግዚአብሔር የመጀመሪያው ውጥኑ የተመለስን የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅሬታ ነን—መዝ. 126፡ 1-4፡-

1. እንደ የእግዚአብሔር ቅሬታ እዚህ የቆምን እና ወደ መጀመሪያው የአንድነት መቆሚያ ስፍራ የተመለስን የክርስቶስ አካል ብልቶች ነን—ዘዳ. 12፡5።

2. አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በምርኮ ውስጥ ቀርተዋል፤ ጥቂት ቅሬታዎች ብቻ ለእግዚአብሔር ግንባታ ወደ ተገቢው መቆሚያ ስፍራ ተመልሰዋል—ቁ. 11፤ 16፡2፤ መዝ. 132፡13-14።

ሐ. የእስራኤል ልጆች ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸው ለክርስቶስ መምጣት መንገድን አዘጋጅቷል—ሚክ. 5፡2፤ ማቴ. 2፡4-6፤ ሉቃ. 2፡4-7፡-

1. የጌታ የመጀመሪያ መምጣት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮኝነታቸው ወደ ቅድስቲቱ ምድር በመመለሳቸው ላይ የተመረኮዘ ነበር፡-

ሀ. በሚክያስ 5፡2 ባለው ትንቢት መሠረት፣ ክርስቶስ በቤተልሔም መወለድ ነበረበት።

ለ. ይህ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በቅድስቲቱ ምድር ውስጥ መኖር ነበረባቸው—ማቴ. 2፡4-6፤ ሉቃ. 2፡4-7።

ሐ. የተመለሱት ምርኮኞች ቅሬታ እግዚአብሔር መቅደሱን እንደገና ለመገንባት እና ለክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት የተጠቀመበት መሣሪያው ነበር—ሚክ. 5፡2።

መ. ቅሬታው ወደ ቅድስቲቱ ምድር ባይመለስ ኖሮ፣ ክርስቶስ በተሠግዎ ወደ ምድር ለመምጣት ምንም መንገድ አይኖረውም ነበር—ሉቃ. 1፡35፤ 2፡4-7።

2. በተመሳሳይ፣ የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ ቤት ግንባታ የአዲስ ኪዳን አማኞች ቅሬታ ከባቢሎን ምርኮኝነታቸው፣ ከዘቀጠው ክርስትና፣ ልዩና-ብቸኛ ወደ ሆነው የአንድነት መቆሚያ ስፍራ በመመለሳቸው ላይ ይመረኮዛል—ኤፌ. 2፡21-22፤ ራእ. 2፡1፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ 1 ጴጥ. 2፡5፡-

ሀ. ጌታ የሕዝቡን ቅሬታ ከባቢሎናውያን ምርኮ በመውጣት እና ወደ ተገቢው የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ በመመለስ ፍላጎቱን እንዲያሚሉለት እየተጣራ ነው—ራእ. 18፡4፤ ኢሳ. 52፡11፤ ኤር. 50፡8፤ 51፡6፤ 9፤ 45።

ለ. የጌታ ውጥን መላውን ክርስትና ለማነቃቃት ሳይሆን ለዓላማው መፈጸም እርሱን ለመከተል እና የአካሉ ክፍል ሆነው ለመገንባት ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆኑ የሕዝቡን ቅሬታ ለመጥራት ነው—ማቴ. 16፡18፤ 18፡17፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡21-22፤ 4፡16፤ ራእ. 1፡11፤ 22፡16።

## V. *ያሕዌ ምለሳን ለእስራኤል ልጆች እንደሚያመጣ ተናግሯል—ኤር. 30፡17፤ 33፡6፡-*

ሀ. ያሕዌ ለኢየሩሳሌም ከተማ ምለሳ እና ፈውስ እንደሚያመጣ ቃል ገብቷል—ቁ. 6።

ለ. የሰላምንና የእውነትን ብዛት እንደሚገልጥላቸው፣ እርሱን ከበደሉበት ኃጢአት ሁሉ እንደሚያነጻቸው እና የበደሉትንና ያመጹበትን ኃጢአታቸውን ይቅር እንደሚል ተናግሯል—ቁ. 6-8።

ሐ. ኢየሩሳሌም በአሕዛብ ሁሉ ፊት የደስታ ስም እና ለእርሱ ምስጋና እና ክብር እንደምትሆን ያሕዌ ተጨማሪ ተስፋን ሰጠ—ቁ. 9።

## VI. የእስራኤል ልጆች ከምርኮ መመለስ የቤተ ክርስቲያንን ምለሳ በምሳሌ ያሳያል—ዕዝ. 1፡3-11፤ ነህ. 2፡11፣ 17፡-

ሀ. ስለ የቤተ ክርስቲያን ምለሳ ስንናገር፣ በመጀመሪያ የሆነ ነገር ነበረ፣ ከዚያም ጠፋ ወይም ተበላሸ፣ አሁን ያንን ነገር ወደ መጀመሪያ ሁኔታው የመመለስ አስፈላጊነት አለ ማለታችን ነው—ማቴ. 16፡18፤ 18፡17።

ለ. በብዙ ምዕተ ዓመታት ታሪኳ ቤተ ክርስቲያን የዘቀጠች በመሆኗ ምክንያት፣ በእግዚአብሔር የመጀመሪያ ውጥን መሠረት ወደ ነበረችበት መመለስ ያስፈልጋታል—1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡27፤ ሮሜ. 12፡4-5፤ 16፡1፤ 4-5፤ ራእ. 1፡11፤ 22፡16።

ሐ. የእስራኤል ልጆች መመለሳቸው ማለት ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ መምጣታቸው ማለት ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ምለሳ በባቢሎን ከተመለከተው ተቆጣጥሮ የራሱ ከሚያደርገው እና የክፍፍል መቆሚያ ስፍራ ከሆነው መመለስን ያካትታል—መዝ. 126፡1-4፤ 133፡1።

መ. የእስራኤል ልጆች ወደ ኢየሩሳሌም፣ እግዚአብሔር ወደወሰነው ልዩና-ብቸኛው መቆሚያ ስፍራ፣ ወደ ባቢሎን ተወስደው ከነበሩት ከእግዚአብሔር የመቅደሱ ዕቃዎች ሁሉ ጋር ተመልሰው ሄዱ—2 ዜና. 36፡18፤ ዕዝ. 5፡14፤ 6፡5፡-

1. ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ሕዝብ እርሱን ያመልኩ ዘንድ ማዕከል ነበረች፣ ይህችም ልዩና-ብቸኛ ማዕከል የእግዚአብሔርን ሕዝብ አንድነት ጠብቃለች፤ ስለዚህም ምክንያት በብሉይ ኪዳን የነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ

ወደ ኢየሩሳሌም፣ በእግዚአብሔር ወደ ተወሰነው ልዩና-ብቸኛ መቆሚያ ስፍራ መመለሳቸው የግድ አስፈላጊ ነበር—ዘዳ. 12፡11፤ 16፡2፤ 26፡2።

2. እነዚህ የብርና የወርቅ ዕቃዎች የክርስቶስን ብልጥግናዎች እና ክርስቶስን የመለማመድ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ያመለክታሉ—ኤፌ. 3፡8።
3. የዛሬው ባቢሎን የእግዚአብሔርን ሕዝብ መማረክ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር መቅደስም ሁሉንም ብልጥግናዎች ዘርፏል፤ ጌታ አሁን ታማኝ ሕዝቡን ከባቢሎን መጥራት እና ተገቢ ወደሆነው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት መመለስ ብቻ ሳይሆን ጠፍተው የነበሩትን የተለያዩ የክርስቶስ ገጽታዎችን ሁሉ መመለስ ይፈልጋል—ቁ. 17-19፤ ቆላ. 1፡15-20፤ 2፡16-17፤ 3፡4።

ሠ. የቤተ ክርስቲያን ምለሳ በኢየሩሳሌም ባለው በእግዚአብሔር ቤት፣ በእግዚአብሔር መቅደስ እንደገና መገንባት እና በኢየሩሳሌም ከተማ እንደገና መገንባት ተመስሏል—ዕዝ. 1፡3፤ ነህ. 2፡11፣ 17፤ መዝ. 26፡8፤ 36፡8-9፤ 46፡1፣ 5፤ 47፡2፣ 6-8፡-

1. መቅደሱ፣ እግዚአብሔር የሚገኝበት ስፍራ ጥበቃ አስፈልጎት ነበር፤ የከተማይቱ ቅጥር የመቅደሱ መከላከያ ነበር።
2. በአዲስ ኪዳን ያለውን የቤቱን እና የከተማዋን ግንኙነት ለመረዳት፣ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መተለቅ እና የክርስቶስ መጨመር መሆኗን ልንገነዘብ ያስፈልጋል—ዮሐ. 3፡29-30፤ ኤፌ. 4፡13፤ ቆላ. 2፡19፡-
   ሀ. የክርስቶስ መተለቅ የመጀመሪያው ደረጃ የክርስቶስ መጨመር ለመሆን ከአማኞች ሁሉ በአንድ ላይ የተዋቀረች ቤቱ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ናት—ኤፌ. 2፡21-22።
   ለ. የክርስቶስ መተለቅ ሁለተኛው ደረጃ ከተማይቱ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ናት፣ ቤቱ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከተማይቱ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ለመሆን መተለቅ አለባት—ማቴ. 5፡14፤ ራእ. 3፡7፣ 12፤ 21፡9-10።
   ሐ. ቤቱ እና ከተማይቱ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ግንባታ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ ማዕከል ነው—ኤፌ. 2፡21-22፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ ራእ. 21፡2-3።
3. ከታላቂቱ ባቢሎን ወደ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የእግዚአብሔር ሕዝብ ምለሳ ከሌለ፣ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣቱን ለመፈጸም ምንም መንገድ አይኖረውም—1፡7፡-
   ሀ. በመጨረሻው ጊዜ ጌታ የቤተ ክርስቲያን ምለሳ እንዲኖረው እየሠራ ያለው ለዚህ ነው—ቁ. 11፤ 3፡7-10፤ 22፡16፤ 1 ቆሮ. 12፡27፤ 1፡2።
   ለ. ይህ ምለሳ ለክርስቶስ ዳግም መምጣት ዝግጅት እና መሠረት ይሆናል—ራእ. 1፡7፣ 3፡11፤ 19፡7-9፤ 22፡7፣ 12፣ 20።

*© 2020 Living Stream Ministry*